

# አህያ ሆኖ የተወለደው ልጅ


Lindiwe Matshikiza
Meghan Judge
Dawit Girma

Amharic
Level 3



አንዲት ህጻን ልጅ አንድ የሆነ አስገራሚ ቅርጽ ከርቀት ተመለከተች።



ያ ቅርጽ እየቀረበ ሲመጣ ድርስ እርጉዝ ሴት መሆኗን ህጻኗ ተረዳች።



ዓይንአፋር ግን ደግሞ ኅበዝ የሆነችው ይህች ህጻን እርጉዟን ሴትዮ ተጠጋቻት። ‹‹ይህችን ሴት ከእኛ ጋር ማኖር አለብን›› በማለት የህጻኗ ቤተ ዘመዶች ወሰኑ። ‹‹እሷን ከእኛ ጋር እናኖራታለን፤ ልጇንም እንንከባከባለን።››



ወዲያው ምጥ ጀመራት። ‹‹ግፊ!›› ‹‹ብርድ ልብስ አምጡ!›› ‹‹ውሃ!›› ‹‹ግፊፊፊፊፊ!!!››



ነገር ግን ህጻኑን ሲያዩ ሁሉም በድንጋጤ ወደኋላ አፈገፈጉ።
‹‹አህያ?!››



ሁሉም መከራከር ያዘ። ‹‹እናትና ልጇን እንንከባከባለን ብለን ቃል ገብተን ነበር፤ አሁንም ቢሆን ማድረግ ያለብን እሱን ነው።›› ሲሉ አንዳንዶቹ፤ ሌሎቹ ደግሞ ‹‹ግን መጥፎ እድል ሊያመጡብን ይችላሉ›› አሉ።



በመሆኑም ሴትዮዋ እንደገና ብቸኝነት ተሰማት። ሴትዮዋ ግራ ተጋባች፤ ይህንን ያልተጠበቀ ፍጡር ምን እንደምታደርገው ጨነቃት። ምን ማድረግ እንዳለባት አላወቀችም፣ በጣም ተወዛገበች።



በስተመጨረሻም ፍጡሩ ልጇ መሆኑንና እሷም እናቱ መሆኗን አምና ተቀበለች።



አሁን ነገሮች ሁሉ አስቸጋሪ እየሆኑ መጥተዋል። ልጁ እንደተወለደ ባለው የአካል መጠን በዚያው ቢቀጥል ልዩ ነገር ነው የሚሆነው። ሲያድግም ለናትየዋ ለመንከባከብ፣ ለማዘል ይቸግራታል። የሆነ ሆኖ ህጻኑ አህያ ለእናትየዋ በጀርባዋ ማዘል እስኪያቅታት ድረስ እያደገ መጣ። እናም ልጁ የጣረውን ያህል ቢጥር ልክ እንደሰው ያለ ባህርይ ሊኖረው አልተቻለውም። እናትየዋም እየደከማት እየፈራችም መጣች። አንዳንዴ እንስሳት እንደሚሰሩት ያለ ስራ እንዲሰራ ታደርገዋለች።



አህያው በውስጡ ግራ መጋባትና ብስጭት እያየለበት መጣ። ይህንና ያንን ማድረግ ላይኖርበት ይችላል፤ እንደዚህ መምሰል እንደዛም መምሰል አይኖርበትም። በዚህ መወዛገብ ውስጥ ሆኖ ይናደዳል፤ አንድ ቀን እናቱን በርግጫ መታትና ከመሬት ጋር አጋጫት።



አህያው በጣም ሃፍረት ተሰማው። ከዚያ ሮጠ። የሚችለውን ያህል ፈጥኖ በጣም ሩቅ ወደሆነ ቦታ ፈረጠጠ።



መሮጡን ሲያቆም መሸቶ ነበር፣ በዚህም አጋጣሚ አህያው ጠፋ። ‹‹ሃ ሂሃ ሂሃ›› አህያው ጨለማው ውስጥ አስካካ። ‹‹ሃ ሂሃ ሂሃ›› ይላል ደግሞ። ግን የገደል ማሚቶው ብቻ ያስተጋባል። ብቻውን ሆነ። ከባድ የድካም ስሜት እንደተጫነው ጥቅልል ብሎ ተኛ።



አህያው ሲነቃ እንግዳ ሽማግሌ ሰውዬ አፍጥጦ ሲያየው አገኘ።
ሽማግሌውን ዓይን ዓይኑን እያየ የተስፋ ጭላንጭል ተሰማው።



አህያው እንዴት መኖር እንደሚገባው የተለያዩ ዘዴዎችን ካስተማረው ከሽማግሌው ሰውዬ ጋር ለመቆዬት አብሮ ሄደ። አህያው በደንብ ያዳምጣል። ትምህርት ይወስዳል። ሽማግሌው ሰውዬም እንደዚያው። እርስበርሳቸው ይረዳዳሉ፤ ይሳሳቃሉም።



አንድ ቀን ማለዳ ሽማግሌው ሰውዬ አህያውን ተሸክመህ ወደ ተራራ ጫፍ አውጣኝ ሲል ጠየቀው።



ተራራው ጫፍ ላይ በደመናው መሃል እንቅልፍ ወሰዳቸው። አህያው በህልሙ እናቱን እንዳመማትና ስትጠራው አየ። እንደነቃ....



… ደመናው ጠፍቷል፣ ከጓደኛው ከሽማግሌው ሰውዬ ጋር።



አህያ በስተመጨረሻም ምን ማድረግ እንዳለበት አወቀ።



አህያው እናቱን ብቻዋን ሆና በጠፋው ልጇ እያዘነች አገኛት። ለረጂም ጊዜ ፍጥጥ ብለው ተያዩ። ከዚያም ጥብቅብቅ ብለው ተቃቀፉ።



ትንሹ አህያና እናቱ አብረው መኖርና ማደግ ጀመሩ። ህይወታቸውን አብረው ማስቀጠል የሚችሉባቸውን በርካታ መንገዶችም አሰቡ። ቀስ በቀስ ሌሎች ሰዎችና ቤተዘመዶች ተረጋግተው ህይወታቸውን መግፋት ጀመሩ።

# Storybooks Jamaica

global-asp.github.io/storybooks-jamaica

## አህያ ሆኖ የተወለደው ልጅ

Written by: Lindiwe Matshikiza
Illustrated by: Meghan Judge
Translated by: Dawit Girma

This story originates from the African Storybook (africanstorybook.org) and is brought to you by Storybooks Jamaica in an effort to provide children's stories in Jamaica's many languages.

This work is licensed under a Creative Commons
Attribution 4.0 International License.